በጉምሩክ ኮሚሽን
የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
CUSTOMS COMMISSION
ADDIS ABABA KALITI CUSTOMS BRANCH OFFICE
የሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት የውስጥ ማስታወሻ

ቁጥር፡ ስ/አ/ጽ/ቤት 105/12

ቀን:14/07/2012 ዓ.ም

ለ፡- የተተዉና የተወረሱ መጋዘን አስተዳደር የስራ ሂደት
ለ፡- ትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር የስራ ሂደት
ለ፡- ንግድ ገቢ ዕቃዎች አወጣጥ የስራ ሂደት
ለ፡- ወጪና ንግድ ያልሆኑ የገቢ ዕቃዎች የስራ ሂደት
ለ፡- ኢስተርን ኢንዱስትሪ ፓርክ የጉ/ሥ/ሥ/ አ/የስራ ሂደት
ለ፡- ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ የጉ/ሥ/ሥ/ አ/የስራ ሂደት
ለ፡- ኢንተለጀንስና ኮንትሮባንድ ክትትል የሥራ ሂደት
ለ፡- ለቡ ኢንዱስትሪ ፓርክ የጉ/ሥ/ሥ/ አ/የስራ ሂደት
ለ፡- ገላን ጉምሩክ መቅረጫ ጣቢያ
ለ፡- የውስጥ ኦዲት ቡድን

ከ፡- ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
አ.አ. ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

አለማየሁ አንቲቾ ደደቦ
ስራ አስኪያጅ
Alemayehu Anticho dedebo
Manager

ጉዳዩ፡- የፀደቁ መመሪያዎችን ይመለከታል፤

የጉምሩክ ኮሚሽን በቁጥር 4.0/0408/68/2012 ዓ.ም በቀን 07/07/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ከገቢዎች ሚኒስቴር በቁጥር 1/160/12 በቀን 07/07/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የጉምሩክ ዕቃ አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 167/2012 እና የጉምሩክ ትራዚት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 168/2012 ለአፈጻጸም የላከለት መሆኑን በመጥቀስ ለአፈጻጸም ልኮልናል፡፡

ስለሆነም መመሪያዎቹን የሚመለከተቸው አመራሮች እና ፈጻሚዎች እንዲያውቁት ተደርጎ በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲፈጸም እያሳሰብኩ ለአፈጻጸም ይረዳችሁ ዘንድ 33 ገጽ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ

ለ፡- ም/ስራ አስኪያጅ (አምራች ወጪና ሌሎች ጣቢያዎች)
ለ፡- ም/ስራ አስኪያጅ (የንግድ ገቢ ዕቃዎች ኦፕሬሽን)
ለ፡- ም/ስራ አስኪያጅ (ህግ ተገዥነት)
ለ፡- ም/ስራ አስኪያጅ (አቅምና ግንባታ ድጋፍ)
ለ፡- ደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ የስራ ሂደት
አ.አ. ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF REVENUES

ጉትን 343
03/07/12

ቀን መጋቢት 0 1 2012
Date
ቁጥር 1/160/12
Ref.No

ጉምሩክ ኮሚሽን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ:- መመሪያ ስለመላክ፣

የጉምሩክ ዕቃ አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 167/2012 እና የጉምሩክ ትራንዚት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 168/2012 ከዚህ ጋር በማያያዝ የላክንላችሁ ስለሆነ በመመሪያዎቹ መሠረት እንዲፈፀም አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

አዳነች አቤቤ
ሚኒስትር

ግልባጭ:-

ለህግ ተገዢነት ዘርፍ

ገቢዎች ሚኒስቴር

Phone: +251 11 662 98 00/ 01/02/03/04/05/06/07/08 Fax: /+251 11 662 98 17
face book page: ministry of revenues. FBP: mor Ethiopia Twitter: erca@twitt
web site: http//www:erca.gov.et P.o. Box: 2559 Addis Ababa, Ethiopia

10/
አ/ሐ

# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የጉምሩክ ኮሚሽን
# THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
# CUSTOMS COMMISSION

ቀን መጋቢት 0 7 2012
Date
ቁጥር 4-0/0408/12
Ref.No.

በአባሪው ለተዘረዘሩት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡ <u>የፀደቀ መመሪያ ስለመላክ፤</u>

የገቢዎች ሚኒስቴር በቁጥር 1/160/12 መጋቢት 01 ቀን 2012 በተጻፈ ደብዳቤ የጉምሩክ ዕቃ አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 167/2012 እና የጉምሩክ ትራንዚት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 168/2012 በመላክ እንዲፈፀም አሳውቋል።

በመሆኑም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፀድቆ በተላኩት የጉምሩክ ዕቃ አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 167/2012 እና የጉምሩክ ትራንዚት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 168/2012 መሠረት አገልግሎት እንዲሰጥ የመመሪዎቹን 32 ገጽ አባሪ በማድረግ የተላከ መሆኑን እናሳውቃለን።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን
ቁጥር 1
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Customs Commission No.1

ከሠላምታ ጋር

ወንድወሰን ደገፋ ካሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን የጽ/ቤት ኃላፊ

<u>ግልባጭ</u>
- ለጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ
- ለትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
  <u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>



☎ +251 116 62 98 00
+251 116 62 98 19
✉ 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>አዲስ አበባ</u>
- ለሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ሞጆ</u>
- ለአዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>አዳማ</u>
- ለድሬዳዋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ድሬዳዋ</u>
- ለጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ጅግጅጋ</u>
- ለሀዋሳ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ሀዋሳ</u>
- ለጅማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ጅማ</u>
- ለሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ሞያሌ</u>
- ለአዋሽ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>አዋሽ</u>
- ለጋላፊ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ጋላፊ</u>
- ለኮምቦልቻ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ኮምቦልቻ</u>
- ለመቀሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>መቀሌ</u>
- ለባህር ዳር ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  <u>ባህርዳር</u>

# የጉምሩክ ዕቃ አወጋገድ መመሪያ ቁጥር

# 167/2012

ገቢዎች ሚኒስቴር

የካቲት 2012

Ethiopian Customs Commission
Records Documentation No.1

# የጉምሩክ ዕቃ አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 167/2012

ኮሚሽኑ የተተወ ወይም በጊዜ ገደቡ ከጊዜያዊ ዕቃ መከማቻ ያልወጣ ወይም የተወረሰ ዕቃ ማስወገድ እንደሚችል በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 የተደነገገ በመሆኑ፤

በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ያሉ ዕቃዎች የሚወገዱበትን ሁኔታ መወሰን እና ወጥ የሆነ የዕቃ አወጋገድ ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የገቢዎች ሚኒስቴር በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 61፣ 62 እና 180 (2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የጉምሩክ ዕቃ አወጋገድ መመሪያ ቁጥር 167/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም፡-

1/ "የተተወ ዕቃ" ማለት አስመጪው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ፈጽሞ እንደማይረከበው የጽሑፍ ማረጋገጫ የሰጠበት ወይም የመጋዘን የቆይታ ጊዜ ገደብ ያለፈበት ዕቃ ነው፡፡

2/ "የተወረሰ ዕቃ" ማለት የጉምሩክ ህግ በመተላለፍ ጥፋት የተፈጸመበትና በጉምሩክ የተወረሰ ዕቃ ማለት ነው፡፡

3/ "አደገኛ ዕቃ" ማለት በሰው ወይም እንስሳት ሕይወት ላይ እንዲሁም በእፅዋት ላይ አደጋ የሚያስከትል መሆኑ ማረጋገጫ የቀረበበት ዕቃ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መጻሕፍትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Customs Commission
Resource & Documentation No. 1